# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ጥር 28 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**መለስ ዜናዊ በኢትዮ-ኤርትራ ውጊያ ላይ በሞቱት ወገኖቻችን ላይ ተሳለቀ፤**

**ነጋዴዎቹን ለመቅጣት አንገት መቅላት ሳይሆን እድሜ ልክ ማሰቃየት ነው አለ፤**

**በአፍሪከ የመሪዎች ጉባኤ ወቅት ሕዝቡ እንግልት ደረሰበት፤**

**የአፍሪካ መሪዎች የህዝባቸውን ድምጽ አክብረው ስልጣን ሊለቁ ይገባል ተባለ**

ሐሙስ ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የወያኔ ጀሌዎች ለተሰበሰቡበት የተወካዮች ምክር ቤት ተብዬ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያበሳጭ አልፎ ተርፎ መስዋዕትነት የከፈለበትን ሁሉ መና የሚያስቀር ንግግር ማቅረቡ ተደመጠ።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሐሙስ ዕለት ከምክር ቤት አባሎች ለቀረቡ ጥያቄዎች ማብራሪያ ሰጠ በተባለበት ወቅት ሲናገር እንደተደመጠው እስከ ዛሬ ለ20 ዓመታት በህዝቡ ላይ ሲጨፍርበት እና ሲያንገላታው ከመኖሩም በላይ አሁን ደግሞ መላ የሀገሪቱን ህዝቦች ሲያንቋሽሽ እና ሲያብጠለጥል እንደነበር ተደምጦዋል።

ከምክር ቤት አባሎች ቀረቡ የተባሉ 20 ጥያቄዎችን መልስ ሰጠ በተባለበት ወቅት ከወያኔ አሽርጋጅ ከሆነው ከዶክተር አሸብር በኩል በአሰብ ወደብ ለመጠቀም የሚያዳግተን ነገር ምንድነው? የድንበር መካለሉስ ምን ደረጃ ደረሰ ? የሚል ጥያቄ ተጠይቆ ሲመልስ « በኤርትራና በእኛ መሀከል የአለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የተዛባ ነው በመሆኑም እንደ ቁማር በሳንቲም ትርታ መለየት ብቻ ካልሆነ ሌላ መፍትሔ የለውም» ሲል ከ80 ሺህ በላይ የኢትዮጵያ ዜጎች የሞቱበትን እና መስዋዕትነት የከፈሉበትን የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እና ድንበር ማካለል ተሳልቆ ምላሽ ሰጥቶዋል፡፡

ህዝቡን እና ሀገሪቱን እየተሳደበ አልፎ ተርፎ ለተሳዳቢ ሲሰጥ የኖረው የወያኔው አለቃ መለስ ዜናዊ በዚሁ በሰጠው ማብራሪያ ላይ እንዳለው ከሆነ የንግዱን ህብረተሰብ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ያስጠነቀቀ ከመሆኑም በተጨማሪ አንገት መቅላት ሳይሆን ማስተማር ነው እያለ እድሜ ልክ እስራት እየፈረደ ከሞት በማይተናነስ ሁኔታ አስሮ ለማሰቃየት እቅድ እንዳለው በግልፅ መናገሩም ተደምጦዋል፡፡

አስቀድሞ የዓለም አቀፍ ህግ ድጋፍ ሳይኖረው እና ከኢትዮጵያ ህዝብ እውቅና ውጭ ወደብ ቆርሶ የሰጠው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ብዙ ሺህ ዜጎች መስዋዕትነት የከፈሉበትን ድል መና አስቀርቶ ለሻዕቢያ በሚሆን መልኩ አመቻችቶ ከጨረሰ በሁዋላ ዛሬ ደርሶ የሀገር ወዳድ ለመምሰል የአሰብ ወደብን እንዳንጠቀም የሻዕቢያ ቡድን ከእኛ ጋር ተባብሮ ለመስራት አይፈልግም በማለት ማብራሪያ መስጠቱ በህዝቡ ዘንድ ከኑሮ ውድነቱ የበለጠ የሰጠው መልስ የእግር እሳት እንደሆነበት ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በሁለቱ ቡድኖች መሀከል እስከ ዛሬ መነሻው ያልታወቀበት እና በግልጽ ባልተነገረበት የሻዕቢያና የወያኔ ጦርነት ከ80 ሺህ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ቀርጥፎ የበላበት ጦርነት ከተደረገበት ግዜ ጀምሮ እርስ በርስ ሲወነጃጀሉ የኖሩ ሲሆን ሰሞኑንም የመላው ኢትዮጵያን ህዝብ ትኩረት ለመሳብ ይሁን በሌላ ምክንያት የሻዕቢያ ቡድን በአዲስ አበባ ከተማ ትላልቅ ፍንዳታዎች ለማድረግ በሚኒባስ ፈንጂ እና ቦምቦችን ጭኖ ሲያስገባ ባቲ ላይ መያዙን የገለፀው መለስ የድረሱልን ጥሪም ለህዝቡ ማቅረቡ ተደምጦዋል፡፡

በተለይ በቅርቡ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔ ሊደረግ ጥቂት ቀናት ሲቀረው ጀምሮ አደጋ ሊጣል ነው የሚል መረጃዎች ከውጭ ሀገር ሲሰራጩ የነበረ መሆኑን የጠቀሱት የወያኔ የምክር ቤት አባሎች እናንተ ግን አንዳችም መልስ ስትሰጡ አልተደመጠም ለምን ይሄ ሆነ? ብለው ለጠየቁት ሲመልስ የሻዕቢያ ቡድን በእኛ ላይ ጥቃት ለማድረስ ሲቁዋምጥ የመጀመሪያው አይደለም ወደፊትም ሊሞክር ይችላል ግን አይሳካለትም ካለ በሁዋላ በሰሞኑም የመሪዎቹ ስብሰባ ከመደረጉ በፊት ወይም በሁዋላ አደጋ ለመጣል በሚኒባስ የተጫነ ፈንጂ እና ቦምብ ጭኖ ሲገባ ባቲ ላይ የተያዘ መሆኑን ገልፆ ይሄም የደህንነት ሰራተኞቻችንን ጥንካሬ የሚያሳይ ነው ሲል በአንድ በኩል ህዝቡን ሊያስፈራራ መከጀሉም ታውቆዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ለብዙ ዓመታት ነዋሪ የሆኑ የኢትዮጵያ ሱማሌዎች የአልቃይዳ ቡድን ሊጠቀምባቸው ይችላል በሚል የመሪዎቹ ስብሰባ ሊደረጉ ጥቂት ቀናት ሲቀረው ጀምሮ ከሚኖሩበት

ሰፈር እየታፈሱ ለእስር ሲዳረጉ የነበሩ መሆኑ እየታወቀ ዛሬ የሻዕቢያ ቡድን ጥቃት ሊያደርስ ሲል ተያዘ ብሎ መግለጫ መስጠቱ የወያኔ ድርጊት እና መግለጫ እርስ በርሱ የተጣረሰ መሆኑን ያሳያል የሚሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ብዙዎች ናቸው፡፡

ከየጎዳናው ላይ እያፈሰ ለእስር የዳረጋቸው ኢትዮጵያዊ ሱማሌዎች በርሀብ እና በውሀ ጥም እያሰቃያቸው እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ አስሮ እያንገላታቸው ባለበት በአሁኑ ወቅት ችግሩን ሊያደርስ የነበረው የሻዕቢያ ቡድን ነው ብሎ መግለጫ መስጠቱ በሱማሌዎቹ ላይ ጥላቻ ብቻ እንዳለበትና በቂ የመረጃ አቅርቦት የሌለው ባዶ ቡድን መሆኑን ያመላከተ መሆኑ ተረጋግጦዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ከህዝቡ ላይ እየዘረፈ እና እየቦጠቦጠ ሀገሪቱን ባዶ ባደረገበት ወቅት በአምስት ዓመቱ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከፍተኛ ለውጥ እናመጣለን እያለ መደስኮሩ የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ህዝቡ በኑሮ ውድነት እግር ከወርች ታስሮ አልላውስ ባለበት ግዜ እድገት ተመዝግቦዋል ከእንግሊዝም ሆነ ከአሜሪካ የተሻለ የበጀት ክምችት አለን እያለ በልበ ድፍንነት እና በማን አለብኝነት ሲደነፋ መዋሉን ተከትሎ ህዝቡ እጅግ ከማዘኑም በላይ በንዴት ቁጣውን ውስጥ ውስጡን እየገለጸ ይገኛል፡፡

የነዳጅ ዋጋ እያሻቀበ ከህዝቡ መግዛት አቅም በላይ በሆነበት በአሁኑ ወቅት አንዳችም ድጎማ ሳያደርግ አሁንም በቅርቡ ዋጋው እንደሚጨምር በይፋ ያለ ሀፍረት በገለፀበት በዚህ ግዜ በህዝቡና በነጋዴው ላይ ብቻ ጣቱን እየቀሰረ መገኘቱ የወያኔ ቡድን የውድቀቱ መጀመሪያ ነው ያሉት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በተለይ ለነጋዴዎች የሰጠው ማስፈራሪያ የሚያሳዝን እና የራሱን ጥፋት በእነሱ ላይ ለማላከክ ብሎም ከህዝብ ጋር ለማጋጨት ያደረገው ጥረት መሆኑን አጋልጠዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በአስመጪነት እና በአከፋፋይነት ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው ያሉትን ነጋዴዎች በአጭር ግዜ የህዝቡን ጥያቄ መመለስ እስካልቻሉ ድረስ እድሉን ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች እንሰጣለን እያለ ከማስፈራራቱም በተጨማሪ ይሄንን የማይፈጽም ነጋዴ ከሜዳው ውጭ እንደወጣ ሊቆጠር ይችላል እያለ የራሱን ሸክም በነጋዴዎቹ ላይ ከመጣሉም በላይ በሌባ ጣቱ እየጠቆመ ሲያስፈራራ እንደነበር ታይቶዋል፡፡

በንግዱ ስራ ላይ ተሰማርቶ በአስመጪነት... በአከፋፋይነት... በአምራችነት እና በሻጭነት የሀገሪቱን 60 በመቶ ንግድ እንቅስቃሴ ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ ጉና ..... ትራንስ......አምባሰል.....በአጠቃላይ ከ42 በላይ ግዙፍ ኩባንያዎችን ያቀፈውን ኤፈርት የተሰኘውን ድርጅት ከህዝብ በዘረፈው ገንዘብ አቋቁሞ ስራ ላይ ባለበት በአሁኑ ግዜ በግል ንግድ ላይ ያሉትን ነጋዴዎች ብቻ ለማጥቃት እና እራሱ የሰራቸውን ወንጀሎች እና እየሰራቸው ያለውን ጋጠ ወጥ ድርጊት ሊያሳብብ መሞከሩ ግዜው ያለፈበት የልጆች ጨዋታ ከመሆኑ አልፎ ህዝቡን ከነጋዴው ሊያጋጭ እና አመጹን የእርስ በርስ ለማድረግ የታሰበ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

በተያያዘ ዜና ሰሞኑን የወያኔው ቀኝ እጅ የሆነው የአዲስ አበባ መስተዳድር ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ነጋዴዎችን ሰብስቦ ባነጋገረበት ወቅት ብሶት የወለደው ቁጣ ሲያስተናግድ እንደዋለ ተሰማ፡፡

የአዲስ አበባን የንግዱ ማህበረሰብ ለማወያየት በሚል በጠራው በዚሁ ስብሰባ ላይ ነጋዴዎቹ በንዴት ወያኔ ላደረሰብን ኪሳራ ካሳ ሊከፍል ይገባል.....ያሉ ሲሆን ለህዝብ የሚያስብ ከሆነ የቀረጥ ክፍያውንም ማንሳት አለበት ሲሉ በጥያቄ አጣድፈውታል።

በአሁኑ ሰዓት የኑሮ ውድነቱ እየሰፋ እና እያደገ በመምጣት ላይ በመሆኑ አስቸኳዋይ የእርምት እርምጃ ማስተካከያ ካልተወሰደ በሌሎች ሀገራት የተነሳው አመጽ በእኛም ሀገር የማይነሳበት ምክንያት አይታየንም ያሉት ነጋዴዎቹ አሁንም እናበንተ ባለስልጣናት ውስጣችሁን መፈተሽ ግድ ይላችሁዋል ሲሉ በምሬት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

የነጋዴዎቹን ቁጣ ሲያዳምጥ የነበረው ኩማ ደመቅሳ በበኩሉ የካሳ ክፍያም አናደርግም የቀረጥ ክፍያውም አይነሳ ካለ በሁዋላ ለሚመጣው የህዝብ አመጽ ሁሉ እናንተ ናችሁ ተጠያቂው ሲልም ለማስፈራራት ሲሞክር እንደነበረና ስብሰባው ያለመግባባት መጠናቀቁ ታውቆዋል።

በሌላ ዜና 16ኛው የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ስቃይ እና እንግልት ሲደርስ እንደሰነበተ ታወቀ። ወያኔ በፈጠረው ችግር ሳቢያ ምንም በማያውቀውና በንጹሀን ዜጎች እንዲሁም በስብሰባ አዳራሹ አቅራቢያ ነዋሪ የሆኑ ዜጎች ላይ ሲወጡና ሲገቡ ከማስፈራራት አልፎ ከፍተኛ ድብደባ ሲፈጸምባቸው እንደሰነበቱ ለማየት ተችሎዋል።

በከተማዋ የተለያዩ አደባባዮች ላይ ድንገት ሳይታሰብ የፌዴራል ፖሊሶች እየመጡ ህዝቡን አንድ ላይ አፍሰው በተገኘው ጉረና ውስጥ እንዲገባ ከማስገደዳቸውም በተጨማሪ ለምን ብሎ ጥያቄ ያነሳውን ሰው በሰደፍ እና ጀርመን ሰራሽ በሆነው ቆመጥ  ሲደበድቡ እንደነበር ታይቶዋል።

ህዝቡ ወደ ስራም ሆነ ከስራ መልስ ወደ ቤቱ ለመሄድ አደባባይ አቁዋርጦ መጉዋዝ ግድ የሚለው መሆኑን የሚያውቁት የወያኔ የደህንነት ባለስልጣናት በውስጣቸው ባለው የህዝብ ጥላቻ ብቻ ህዝቡ በአደባባይ ላይ እንዳያልፍ እና በመንገዶች ላይ ዝር እንዳይል  ከማድረጋቸው በተጨማሪ ግድ በዚያ መንገድ ማለፍ የሚገባውን ደግሞ እየቀጠቀጡ ለእስር ሲዳርጉ እንደከረሙ ታውቆዋል።

በኑሮ ውድነት እጅግ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እየዳከረ የሚገኘውን ህዝብ እንደገና መንገድ አታልፍም በሚል ቀን ከሌሊት ዘግተው ሲያሰቃዩት ከመክረማቸውም በላይ መደብደባቸው የወያኔ ቡድን ከወዲሁ ፍርሀት ያደረበት በመሆኑ ሊያስፈራራ መሆኑን የጠቆሙት ነዋሪዎች ወያኔ በሱዳን ፤በግብጽ እና በቱኒዚያ የተነሳው አመጽ እያሰጋው እና እያስፈራራው  የሚወስደው እርምጃ ቢሆንም አንድ ቀን ግን አይቀሬ ነው ሲሉ የችግሩ ሰለባዎች በቁጭት ሲገልጹ ተደምጠዋል።

ከእግረኞች በተጨማሪ ተሽከርካሪ የያዙትን ወገኖችም በየቦታው መንገድ ለቅቀው እንዲቆሙና አስፈላጊ ሲሆን ከመኪኖቻቸው እንዲወርዱና በእግራቸው ከሌሎች እግረኞች ጋር እጉሮኖ ውስጥ እንዲገቡ እየተደረገ የቁም ስቃይ ሲያዩ እንደነበር ተረጋግጦዋል።

አንዳችም ለአፍሪካ ህዝቦች ፋይዳ የማያመጡ አምባገነን መሪዎች የተሰበሰቡበት ይሄው ስብሰባ ላይ ድንገት የተገኙት የፈረንሳዩ መሪ ኒኮላስ ሳርኮዚ እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሀፊ

በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተነሱ የህዝብ አመጾችን ከወዲሁ ለህዝባቸው ተገዥ እስካልሆኑ ድረስ ሁሉም ጋር እንደሚመጣ ማስጠንቀቃቸው ታውቆዋል፡፡

የፈረንሳዩ መሪ ሳርኮዚ አሁን እየታየ ያለው የህዝብ ማዕበል በሁላችሁም ጋ ሊመጣ የሚችል በመሆኑ ከወዲሁ የማስተካከያ እርምጃ ስልጣን እስከ መልቀቅ ድረስ መውሰድ እንደሚገባችሁ ልትገነዘቡና ልትጠነቀቁ ይገባችሁዋል ሲሉ ማሳሰቢያ እንደሰጡዋቸው ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ለአፍሪካ ህዝብ አንድም የረባ ውሳኔ ሳያሳልፉ ይልቁንም የህዝብ ድምጽ ሰርቀው በስልጣን ላይ ላሉት መሪዎች ድጋፍ ሲያደርጉ የሰነበቱት እነዚሁ መሪዎች በኮትዲቩዋር ፤በሱዳን ፤በግብጽ እና በሌሎችም ሀገራት ውስጥ እየተደረጉ ያሉትን የህዝብ ትግል አንዱንም ሳይመለከቱና ሳይነጋገሩበት አድበስብሰው ላይ ላዩን ብቻ ሲሮጡ እንደከረሙና እንደተበተኑ ታውቆዋል፡፡

ይሄንኑ የተድበሰበሰ የመሪዎች ስብሰባ የተከታተሉት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሀፊ ባን ኪሙን በበኩላቸው ልክ እንደ ፈረንሳዩ መሪ ሳርኮዚ ሁሉ በአሁኑ ሰዓት በሰሜን አፍሪካ እንደተነሳው የህዝብ አመጽ ሁሉ ወደ ለሌሎቻችሁ ዘንድም የሚዛመት መሆኑን አውቃችሁ የህዝባችሁን ጥያቄ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመመለስ ከወዲሁ ዝግጁ መሆን ይጠበቅባችሁዋል በማለት ከረር እና መመር ያለ ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር መለገሳቸው ተጠቁሞዋል፡፡

በአዲስ አበባ የአፍሪካ የመሪዎች ስብሰባ እየተደረገ ባለበት ሰሞን ከአህጉሩ በእድገት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነን እያሉ የወያኔ መሪዎች ሲያቅራሩ እንዳልነበር በመዲናዋ አዲስ አበባ ጭምር መብራት ለ24 ሰዓት እየጠፋ እንደነበር የተመለከቱ ዲፕሎማቶች ቃልና ተግባር በፍጹም ያልገጠመባት ሀገር መሆንዋን አረጋግጠው መሄዳቸውን ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልጹ ተደምጠዋል፡፡